የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

# ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የተሰጠ ልዩ መግለጫ

ሥልጣን በጠብ-መንጃ ኃይል የያዘው ኢሕአዴግና በሱም የሚመራው የአቶ መለስ ዜናዊ መንግሥት ያለ ሕዝብ ፈቃድና ፍላጎት አሁንም በአመፅና በጉልበት ብቻ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ካለፈው ግንቦት ሰባት ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ምርጫ ጀምሮ በተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች፥ ሕዝብ እንዲወክሉት በመረጣቸው የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ዓይን ያወጣ አፈናውንና የግፍ እርምጃውን ከመውሰድ ካለመቆጠቡም ሌላ መደበኛ ጦር በሰላማዊ ዜጎች ላይ በማዝመት አስከፊ ገጽታውን እያሳየ ይገኛል፡፡ ከትላንት ሌሊት (ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም) ጀምሮ ዛሬ ጧትና ቀኑን ሙሉ በተለይ በአዲስ አበባና በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች የሚደረገው አረመኔአዊ እርምጃ ተጧጡፏል፡፡ ከጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ሌሊቱን ጀምሮ በአሁኑ ጊዜ በአደስ አበባ ሕዝብ ላይ እየተፋፋመ ያለው የኢሕአዴግ አረመኔአዊ ተግባርና በተለይ በቆራጥ የተቃዋሚው ክፍል መሪዎች ላይ እየተደረገ ያለው የግፍ እርምጃ፥ እስራትና ማሳደድ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ እሳዝኗል፥ በተገቢም አስቆጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት አገዛዙ በተያያዘው በዚህ አዲስ ዙር ዘግናኝ እርምጃ የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን በቁጭት ሲገልጽ፥ መስዋዕት የሆኑ ሰማዕት ዜጎቻችንን እየዘከረና በሕዝባችን የመንፈስ ጥንካሬና በታጋይ ልጆቹ ቁርጠኝነት ያለውን ኩራት በማሰብ ነው፡፡

ሕዝባችን ይኸን የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የጅል ዱላ እንደ አንድ ሰው በመሆን በጥናትና በሥነ-ሥርዓት በተደራጀ መልክ ከመታገል ሌላ ምንም አማራጭ የለውም፡፡ የሰላማዊ ትግሉን ይዞታና አቅጣጫ በተመለከተ ቀደም ሲል ኅብረታችን በተከታታይ ጥሪዎች ማድረጉና የተለያዩ አሳቦችን ማስተላለፉ ይታወቃል፡፡
ኢዴኃኅ (ኅብረቱ) አሁን የተከሰተውን አዲስ ዙር ሽብር በሚመለከት በውጭም በውስጥም ያለው ኢትዮጵያዊ በሚከተለው መልክ ጊዜ ሳይሰጥ እንዲንቀሳቀስ ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል፡፡

1. ይኸንን አረመኔአዊ እርምጃ ገዥው ፓርቲ ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲያቆም፤

2. የታሰሩት የድርጅት መሪዎች፥ አባላት፥ ደጋፊዎችና ሰላማዊ ዜጎች ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲለቀቁ፤

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁጥር(Tel.No) 2511-574719;(Fax) 2511574720

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
(Tel.No) 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

3. ከሰላማዊ ፖሊስ ሌላ አገዛዙ ያሰማራቸውን የመደበኛ ሠራዊት ክፍሎች በአስቸኳይ ከከተሞች እንዲወጡ፤

4. የዓለም-አቀፍ የሰብኣዊ መብት ተቆርቋሪ ተቋማት፥ የተባበሩት መንግሥታት፥ የአውሮጳ ኅብረት፥ ወዘተ ... ያሉበት ገለልተኛ ኮሚሽን ባስቸኳይ ተቋቁሞ ይኸንን አረመኔአዊ ድርጊት እንዲያጣራና በተጠያቂዎች ላይ አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ፤ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች አስፈላጊው ካሣ እንዲከፈላቸው፤

5. የዚህ ሁሉ ግፍ ቁንጮ የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ ከሥልጣን እንዲወርዱ፤

6. ትግሉን በፓርላማ ውስጥ መግፋት ይቻላል በሚልና ሌሎች ምክንያቶች በተቃዋሚው ስም በተቋቋመው የኢሕአዴግ ሕገ-ወጥ ፓርላማ የገቡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት አሁን የኢሕአዴግ መንግሥት በሕዝብ ላይ ከሚወስደው አረመኔኣዊና ኢ-ዴሞክራሲያዊ እርምጃ አኳያ ፓርላማ የገቡበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን ከዚህ አሳፋሪ ሥርዓት ጋር እንደቆሙ እንዳያቆጥራቸው አቋማቸውን መርምረውና ያላቸውን ቁርኝት በአስቸኳይ አቋርጠው እራሳቸውን እንዲያገልሉና አሰላለፋቸውን ከታጋዩ ሕዝብ ጋር እንዲያደርጉ፤

7. ሆን ተብሎ አንዱን የሕዝብ ክፍል ከሌላው ጋር ለማጋጨት በአቶ መለስና በግብረ-አበሮቻቸው የሚለፈፈውን ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ሕዝብ የኢንተርሐሞይ ከይሲ ዝባዝንኬ ንቆ በመተው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለመደና ባስመሰከረው ጨዋነቱ፥ እንደሁሌው በድርጅት፥ በጎሣ፥ በሐይማኖት፥ በአካባቢ፥ ወዘተ.... ልዩነት በሌለው ሁኔታ በየአካባቢው የቀውጢ ጊዜ አካል በማቋቋምና በመደራጀት ሰላማዊ ትግሉን እንዲቀጥል፤
በተለይ በአሜሪካ ኤምባሲ፥ በፓርላማ፥ በማስታወቂያ ሚኒስቴር፥ በእንግሊዝ ኤምባሲ፥ እስረኞች በተለይም መሪዎች በታሰሩባቸው ቦታዎች፥ ወዘተ... ዙሪያ በመሰባሰብ በተለመደው ጨዋነትና ሰላማዊ መንገድ የታሰሩት እንዲፈቱ እንዲጠይቅ፥ በተከታታይ ከቅንጅቱና ከኅብረቱ የሚቀርቡለትን ጥያቄዎችና መልእክቶች እንዲከታተልና በተቻለ መጠን በጥንቃቄ ተግባራዊ እንዲያደርግ፥ በገጠርም በከተማም ያለው ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር እንደ አንድ ሰው ሆኖ የጋራ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ፤ ኅብረቱ በትላንትና መግለጫው እንዳስቀመጠው ሁሉ ቅንጅቱ ያቀረባቸውን ቤት ውስጥ የመዋልና ሌሎች ሰላማዊ የትግል ጥሪዎች ሕዝቡ ተቀብሎ ከተለዋዋጭ ሁኔታው ጋር በተጣጣመ መልኩ ተግባራዊ እንዲያደርግ፤

8. በውጭ ያለው ወገን ኢትዮጵያዊ በቅንጅቱና በኅብረቱ አስተናባሪነት በዓለም-አቀፍ ደረጃ የሰላማዊ ሰልፎችና የሻማ ማብራት ተቃውሞና ተማጽኖ ማድረግ፥ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ክፍሎችን፥ የዜና ማሰራጫ ተቋማትን፥ የሰብኣዊ መብት ተሟጋቾችና የሐይማኖት ተቋማትን፥ ወዘተ.. በአካል በማግኘት፥ ስልክ በመደወል ፤ ኢሜይልና ፋክስ በማድረግ፥ ወዘተ.. የታሰሩት መሪዎችና ዜጎች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፥ የአቶ መለሰ ዜናዊ የሽብር ዘመቻ እንዲቆም፥ ወዘተ ... እንዲጠይቅ፤

9. ሕዝባችን በግንቦቱ ምርጫ የተሰረቀበትን ድምፅ ለማስመለስ ብዙ መስዋእትነትን ከፍሏል፥ አሁንም እየከፈለ ይገኛል። ሕዝባችን ይኸን ሁሉ መስዋዕትነት የከፈለው መብቱን አስከብሮ የሥልጣን ምንጭ መሆኑን ለማረጋገጥ ስለሆነ ይኸ እውን እስኪሆን ድረስ ሕዝቡ የጀመረውን ሰላማዊ ትግል ባለማቋረጥ እንዲቀጥልና

ከዚህ መንግሥት ጋር የሚደረጉ ማናቸውም ዓይነት ድርድር ይኸንን መሠረታዊ ዓላማ እንዳይበርዝና ከሕዝቡ ጀርባ እንዳይሆን አስፈላጊው ጥንቃቄ ሁሉ እንዲደረግ፤

10. የኢትዮጵያ ሕዝብ እየታገለ ያለው ድምጼ ይከበርልኝ፥ መብቴ ይጠበቅልኝ የሚል ሰላማዊና ሕጋዊ ጥያቄ እንጅ የአገር ዳር ድንበርና ብሔራዊ ሉኣላዊነትን ማስከበር ያለበት መደበኛ ሠራዊትን የሚያስዘምት ምንም ዓይነት ሕገ-ወጥ ተግባርም ሆነ አሳብ አለመሆኑ ይታወቃል:: የኢትዮጵያ የፀጥታና የጦር ክፍሎች ለአንድ ድርጅት አልፎም ለተወሰኑ ጥቂት ግለሰቦች ሥልጣን መቆየት ሲባል በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደረግ አረመኔኣዊ ተግባር ከመፈጸም እንትቆጠቡ ወገናዊ ጥሪ እያቀረብን ይኸ ሳይሆን ቢቀር አሁን እናንተ በራሳችሁ ዜጎች ላይ እንድትወስዱ በምትጠየቁት አረመኔኣዊ እርምጃ ብቻ ሥልጣናቸውን ለማቆየት የሚፈልጉ ጥቂት መሪዎች ነገ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚያነሳው እናንተን በወንጀለኛነት የመጠየቅ ሕጋዊ ሃላፊነት አብረዋችሁ እንደማይቆሙም ሆነ በምንም መልኩ ዋስትና እንደማይሆኗችሁ ማወቅ እንደሚኖርባችሁ ልናሳስባችሁ እንወዳለን::

11. የኢሕአዴግ ሰፊ አባላትና ደጋፊዎች በአቶ መለስ ዜናዊ መንግሥት በወገን ኢትዮጵያውያን ላይ እየተወሰደ ያለው ይኸ አረመኔኣዊ ተግባር በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ የተወሰደ ፀረ-ሕዝብ እርምጃ በመሆኑ ከቀረው ወገናችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመሆን ለጋራ መብት መከበር አብራችሁ እንድትቆሙ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

የአቶ መለስ አረመኔኣዊ እርምጃ ባስቸኳይ ይቁም!
የታሰሩ መሪዎችና ወገኖች ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ባስቸኳይ ይፈቱ!!
የኢትዮጱያ ሕዝብ መብት በጋራ ሰላማዊ ትግሉ ይከበራል!!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ጊዜም ያሸንፋል!!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ጥቅምት ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም